# አሜሪካንን ያሳስባታል

ዓለማችን ከፍጥረተ መንግሥት ጀምሮ እስከ አሁን በርካታ ኃያላን መንሥታትን አስተናግዳለች። አሁን ባለንበት በእኛ ዘመን ኃያልነቱን አሜሪካ ተረክባ እያቀላጠፈችው ነውና በዚች ምድር ላይ ያሉት እንቅስቃሴዎች ሁሉ አሜሪካንን ያሳስባታል።

የምድራችን ሙቀት መጠን መጨመር፤ የሰብዓዊ መብት አያያዝ የኢራን ኒኩለር ግንባታ፤ የኃይል ምንጮች እንቅስቃሴ፤ ግሎባላይዜሽን፤ የዓለም ኢኮኖሚ መናጋት አሸባሪነት ማስፋፋት፤ የመሳሰሉት ታላላቅ ዓለም አቀፍና የራሷ የውስጥ ችግሮች የአሜሪካ ሐሳቦች ናቸው።

ሰሞኑን ደግሞ ሕወሓት/ወያኔ ማሰርና ማሰቃየት ከተፈቀደለት ኢትዮጵያውያን ውጭ የስውዲን ዜጎችን በማሰሩ ታላቋ አሜሪካን ሓሳብ ላይ ጥሏታል። እኔም ለዛሬው ጽሑፌ መነሻ የሆነኝ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዎ በድጋሚ ጃንዋሪ 10/2012 የአሜሪካን መንግሥት አቋም በማለት የቀረበውን መግለጫ በመመርኮዝ ነው። የታሰሩት የስውዲን ጋዜጠኞች ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞችና በርካታ የፖለቲካ እስረኞች ቢኖሩም የአሜሪካን መንግሥት በተለይ ያሳሰበው የስውዲሾቹ ጉዳይ ብቻ መሆኑ እኛንም ሊያሳስበን ይገባል ብዬ ነው።

በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል ባለው ግንኙነት የሚታሰብለትና የማይታሰብለት ሰውን በግልጽ እንደነገሩን ሁሉ ጉዳያችንና ጉዳቸውም እንዲሁ ተለይቶ ተቀምጧል። ይህንን ማወቅ ደግሞ ለምናደርገው የነፃነት ትግል ጩኸት ይቀንስልናል ኃይልና ጊዜም ይቆጥባል። መቼም በኢትዮጵያ እውነትን የማሳወቅ ትግል ከሰብዓዊ መብት ረገጣ አልፎ አስቂኝ ድራማ እየሆነ መጥቷል። ጋዜጠኛ መረጃ ፍለጋ እንደሰላይ አጠያይቆ፤ እንደዉሻ አነፍንፎ፤ እንደወታደር ዘምቶ፤ እንደወንጀለኛ ታሥሮ ባጠቃላይ እውነትን ፍለጋ በእንባ አስመጭ ቦንብ ጭስ ታጥኖ ለሕዝብ እውነተኛ መረጃ ያዳርሳል። የስውዲን ጋዜጠኞች ያደረጉት ይህንኑ ነው። ለመረጃ፤ ለእውነት፤ አንድ ጋዜጠኛ ሊከፍል የሚገባውን የሙያ ግዴታ እየተወጡ ነው። ይህን ወያኔም፤ የአሜሪካም፤ የስውዲንም መንሥት ጠንቅቀው ያውቁታል። ሁለቱ መንግሥታትና ወያኔ የፍርድ ድራማ ጀመሩ፤ ፍርዱም ተጠናቀቀ። ተውኔቱ ግን ቀጠለ።

ስውዲን ሌላው ቢቀር የአውሮፓን ኅብረት በማስተባበር ለዜጎቿ መፈታት አስቸኳይ የሆነ ጫና ማድረግ ስትችል ክፉኛ ተለሳለሰች። የወያኔም ጦር ነጭ ጋዜጠኛ ከጦር ሜዳ ማረክሁ በማለት ፉከራውን አበዛ። እንኳን ለእነ እስክንድር ነጋ ነጭ ጋዜጠኛ አስራለሁ እያለ ጉሮ ወሸባዬ ያዘፍን ገባ። አሜሪካም ጋዜጠኞቹ ይፈቱ ሳይሆን ጉዳዩ ያሳስበናል አሉ። እኔን ያሳሰበኝ ደግሞ በዚህ ድራማ የሚተላለፈው መልዕክት ነው። አዲስ አበባ ላይ የተደራጀው የለጋሽ አገሮች ማኅበርስ ምነው ድምፁ ጠፋ? ወያኔ ሲጠቃና በምርጫ ሲሸነፍ ብቻ ነው የሚንቀሳቀሰው? ስዊዲንስ የማሕበሩ ዓባል አልነበረችም?
ስውዲን በመላው ዓለም በሳላማዊነቷ የምትታወቅ፤ መልካም ስምና ዝና ያፈራች፤ ለሦስተኛው ዓለም በምትለግሰው ዕርዳታዋ የገነባችው ማንነቷ፤ ለትምህርት፤ ለጤና፤ ለእርሻ የመሳሰሉት ዕድገት ያበረከተችው ተዋፅዖ ከፍተኛ ነው። ለአፍሪቃ አገሮች ነፃነትና ለደቡብ አፍሪቃ ለፀረ አፓርታይድ ትግል ስመ ጥር ልጇን ጠቅላይ ሚኒስትር ኦልፍ ፓልምንእንደገበረች ይታወቃል። ያልተጣራ እውነት ቢባልም ዓለም ተወያይቶበት የአመለካከት አቅጣጫውንውን ያነጣጠረበትና ድምዳሜ ላይ የደረሰበት ጉዳይ ነው። ታዲያ ይህ የስውዲን ወርቃማ ዓለም ዓቀፋዊ ወዳጅነት አንዳንድ ግዙፍ የስለላ ድርጅቶች እጅግ ጥብቅ ለሆነ መረጃ ሥራ በስውዲን ዜጎች እየተጠቀሙባቸው ስለሆነ የስውዲን መንግሥት ሊጠነቀቅበት ይገባል፤ እኛም የዚህ ድራማ እንቆቅልሽ እንዴት እንፈታዋለን? ለማንኛውም ጠርጥር ከኪስህ አይጥፉ" ከፖሊስ አሰልጣኞች የተገኘ ትምህርት) ልስላሴው አላማረኝም።
የአሁኑ የስውዲን መንግሥት መለሳለስና የፍርድ ሂደት እንዲሁም የአሜሪካ ሐሳብ ውስጥ መግባት ድራማ የሚጠቁመው ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕይታ እጅግ የወረደ፤ የተናቀና የተጠላ በመሆኑ ወደፊት አይቀሬ የሆነው የሕዝብ አመጽ ቢነሳ ይህንን ሕዝባዊ ንቀት ለማስቀየር የሥነ ልቡና ጫና በማሳደር ወያኔን በማግዘፍ ማንንም የማሠር ብቃት እንዳለው፤ የመረጃ አቅሙም በምሥራቅ አፍሪቃ ተወዳዳሪ የሌለው አይበገሬ ኃይል አድርጎ በማሳየት ማንም የውጭም ሆነ የውስጥ ጋዜጠኞች ድርሽ እንዳይሉ የማስፈራርያ ድራማ ነው ብለን እንድንገምት ይገፋፋል። ገና ከጅምሩ ጋዜጠኛውና ፊልም አንሺው ከስቶኮልም ተነስተው ሶማሊያ ከዚያም የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጠው ሲገቡና ክላሽን ኮቭ መሣሪያ አጠቃቀም ሲማሩ የተነሱት ቪዲዮ የሚያሳየው በጋዜጠኞች ላይ ጋዜጠኛ፤ በፊልም ቀራጭ ላይ ሌላ ፊልም ቀራጭ ተመድቦ ሲሰራበት ያውም በትጥቅ ትግል በተሠማራ ነፃ አውጪ

ዲስፕሊን እንዴት ተቻለ? ይህንን እንግዲህ ለአንባቢያን ልተወው ወ ደ ሌላው ልሂድ። ልዕለ ኃያል አሜሪካ የዓለም ጉዳይ እንደሚያሳስባት ሁሉ የኢትዮጵያም ጉዳይ ያሳስባታል ስንል፤ የትኛው ጉዳይ በምን ያህል መጠን? ብለን ለያይተን ማወቅ ግድ ነው። አሜሪካ ለኢትዮጵያ መሬት ታስባለች። ምክናያት፡- ለወታደራዊ ጠቀሚታው፤ የኃይል ምንጭነቱና ልዩ ልዩ ያልተዳሰሱት መዐድናት፤ ውኃውና ሌሎችም ተዛማጅ ጉዳዎች በከፍተኛ ሁናቴ ሲያሳስባት በሁለተኛ ደረጃ የሚያሳስባት እንዳሸከር የሚታዘዝላት ወያኔም ሕዝብን ረግጦ አገርን አዋርዶ የሚገዛበት ጉልበቱ እንዳይላላና የሜሪካንን ጥቅምና ቁጥጥር ይዞ በሕዝባዊ አመጽ ተንኮታኩቶ ገደል እንዳይገባ ያሳስባታል። ይህ አይቀሬ ከሆነ ደግሞ እሱን የሚቀይር ሌላ አስተማማኝ አሽከር መንግሥት በተለዋጭነት (ተጠባባቂ መንግሥት) አዘጋጅታለች። ከሰማንም ሰንብተናል። ሦስተኛውና ብዙም አሳሳቢ ያልሆነው ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ነው። እንደሌሎቹ ዐበይት ጉዳዮች አሜሪካንን አያሳስባት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍጹም የአሜሪካ ወደጅ ነበር፤ አሁንም ነው። ድሀ ቢወድ ምንም ባይጥቅምም ቢጠላ ግን ይጎዳል። ድሀ ደግሞ ቆራጥ ነው” እንደ ቱኒዝያዊው “መሐመድ ቧዚዝ” ወይም እንደ ኢትዮጵያዊው “የኔሰው ገብሬ” የኢትዮጵያ ሕዝብ አሜሪካንን ቢውድም አሜሪካ ግን የፍቅር ብሯን ጥርቅም አደርጋ ዘግታበት በወያኔ ጅራፍ ታስገርፈዋለች። ሌላው ቢቀር በቅርቡ በወያኔ መሪነት ሶማልያ ባይዘምትላትና ያንን ክፍተት ወያኔ ባይሸፍነውና የአሜሪካ ጦር ቢዘምት ወጭው፤ ሊፈጠር የሚችለው ዓለም አቀፍና የውስጥ ፖለቲካ ትርምስ፤ የሰው ሕይወት... ወዘተ. ኪሳራ መሸፈኑ በቀላል አይገመትም። ሂሳቡ እንኳን ቢሰላ አሜሪካ ለአንድ ወታደሩዋ ለቼኮሌት ብቻ የምታወጥው መፈናፈኛ ለሌለው የኢትዮጵያ ወታደር የወር ደምወዝ ይሆናል። ይህንን ውለታ አሜሪካ የመዘገበችው በወያኔ ሂሳብ እንጂ በኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም።

ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ሶቪየት ኅብረት ስለ ኢትዮጵያ ብላ ትጨነቅልን ነበር። ሶቪየት ኅብረት ስትፈራርስ አሜሪካ የሌኒንን ሐውልት በቡል ዶዘር አፈራርሳ ወያኔና ሻዕቢያ በመሣሪያነት ኦነግን በማስመሳያነት ሽፋን አድርጋ ስትመጣ ሕዝባችን አሜሪካንን የሚያውቀው በደጉ ዘመን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በነበረው ሁኔታ በመሆኑ ወያኔና ሻዕቢያን ቢጠላም አሜሪካ ኃላፊነት የሚሰማት አገር ስለሆነች እሷን ተማምኖ ተቀበላቸው።

አሜሪካና የኢትዮጵያ ሕዝብ አሥራ ሰባት ዓመታት ተለያይተው ከኖሩ በኋላ በ1983 ሲገናኙ አሜሪካኖቹ እጅግ ተቀይረው ከደግነት ወደ ክፋት፤ ከየዋህነትና ይቅር ባይነት (እርቅ) ወደ ቂምና በቀል ዞር ብለዋል፤ ኢትዮጵያውያን ደግሞ 1966ዓም. የነበረው ወዳጅነት አስተሳሰብ ላይ ቆመዋል። በ1969 ዓም የቃኘውን ጦር ሠፈር፤ የባህር ሠፈራቸውንና የባህል ተቋም በ48 ሰዓት ያስወጣቸውን ወታደራዊ መንግሥት አስታውሰው፤ ወታደር የሆነ ሁሉ ሥራውን እንዲያጣ አደረጉ። የኢትዮጵያን ሠራዊት እንደሌኒን ሐውልት አፈረሱት። በምትኩም የሕወሓትን ተዋጊ የኢትዮጵያ ጦር ብለው ሠየሙት። ወታደራዊ መንግሥት ያንን እርምጃ በወሰደበት ጊዜ የነበረው የቀድሞ ጦርና አብዛኛው ከዚያ በኋላ የተቀጠረ በመሆኑ ከዚያ ጦር ውስጥ ታሪኩን እንኳን የሚያውቁ ጥቂቶች ነበሩ።

በዚያን ጊዜ ሁኔታው ሲከሰት ጀነራል ተፈሪ ባንቲ ከኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ከአሜሪካ ሥልጣን ላይ ነበሩ። ዛሬ የኛ ጀ.ተፈሪ ባንቲ የሉም። የአሜሪካው ካርተር ግን አሉ። ካርተርም በርሳቸው ዘመን የደረሰውን ጥቃት ከዚያም አልፈው ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆን መንግሥቱን ሐራሬ አሥረው የበታቾቹን ወህኒ ቤት ካስቆጠሩ በኋላ በሕይወት የተረፉት ከወህኒ ወጡ፤ ኮለኔሉም ከሐራሬ መጽሐፍ አወጡ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ነፃ አልወጣም።

የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣኖች የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው በምህረት በ20 ዓመታቸው ተፈቱ ከደህንነት ኃላፊው በስተቀር። የፍርዱ ነገር ወያኔ ሲገባ በለንደን ኮንፍረንስ ላይ በውስጣዊ ውል ያለቀ ጉዳይ እንደሆነ የማይስማማ የለም። ማንም ተፈታ ምንም ምዕራባውያን ኢትዮጵያን ለመፍታት አልሞከሩም። ኢትዮጵያ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ሶሻሊዝምን በማወጇ ምዕራባውያንን በማስቀየሟና ባደረሰችባቸው ኪሣራ ስንት ዓመት እንደተፈረደባት ባናውቅም ለመፍታት ግን ፍንጭ እንኳን አላሳዩም። እነሱ መፍታት ባይፈልጉም እስር ቤቱን ሰባብሮ መውጣት የታሣሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ የሌለው ውሳኔ መሆን አለበት።

አሜሪካ መቼም የምታስብበት አታጣምና የኩባ፤ የሰሜን ኮርያ፤ የኢራን፤ ቬንዙዌላ...ወዘተ. ያሳስባታል። ታዲያ ለእነዚህ አገሮች እንደ ኢትዮጵያ ከሆነ የምታስብባቸው የእነሱን የወደፊት ሁኔታ ሳስብ ይሰቀጥጠኛል። ደግነቱ በእነሱ አብዮት ጊዜ የነበሩት ፕሬዚደንት ጆን. ኤፍ ኬኔዲ ወይም ከዚያ በፊት የነበሩ የአሜሪካ መሪዎች ዛሬ በሕይወት የሉም እንጂ እንደ ጂሚ ካርተር ላይ ታች ወጥተው ወርደው ልክ ያገቧቸው ነበር። ለሰሜን ኮርያ እህቷ ደቡብ ኮርያ፤ ለኩባም

አያቷ ስፔንና እህት ወንድም የሆነው ላቲን አሜሪካ እንደ ምሥራቅ ምዕራብ ጀርመን ይተቃቀፋሉ። ተቆርቋሪ አላቸው። እንደ ኢትዮጵያ ብቸኛ አይደሉም።
ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ሰኔና ሰኞ ገጠሙባት፤ ፈጣሪም ፊቱን አዞረባት፡ ከላይ ሆነው ጂሚ ካርተር አጠቃላይ ሲመሩና ሲቆጣጠሩ፡ ከታች ኸርማን ኮኸን ወያኔና ሻዕቢያን ሲያደላድሉ፡የኢትዮጵያን ሕልውና ታሪካዊ ተቀናቃኝ የሆነችው ግብፅ ደግሞ በለስ ቀንቷት ልጃቿ አንዱ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ዶር. ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊን፤ ሌለኛው በአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ሳሊም አሕመድ ሳሊም ሆኑና ተገጣጠመ፤ ሁሉም ነገር ያለ ከልካይና ታዛቢ ተከወነ።
ፕሬዘዳንት ጂሚ ካርተር የሌኒንን ሐውልት አፍርሰው የራሳቸውም የካርተር ማዕከል በቃኘው ምትክ በስማቸው አቁመው፤ አገልጋያቸውን ወያኔን ላገለገሉበት እድሜልክ የአሜሪካ መግቢያ ቪዛ; የእራሳቸው የጅ ፊርማ ያረፈበት ፎቶ ግራፍ ሰጥተው ለመታሰቢያም አብረውም ተነስተው፤ ሸመው ሸልመው ደስ አሰኝተዋቸዋል። ወያኔዎቹ ከቀድሞ ወታደራዊ ሶሻሊስት ባለሥልጣኖች ቢሮ የተሰቀለውን የመንግሥቱንና የነማርክስን ፎቶ አውርደው የእሳቸውን በቦታው ተክተው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ይህም ሥራ እስከ 1997 ግንቦት ወር ድረስ የማይደፈር ተብሎ ይታሰብ ነበር።
አሜሪካኖች በለውጥ ያምናሉና ደግሞም ዕድሜም ተጫጭኗቸል፤ ሰውና እንጨት ተሰባሪ ነውእንዲሉ ከሳቸው የተረፈውን ያልተጠናቀቀ ሥራ ለሌላው ዲሞክራት ፕሬዚደንት ለቢል ክሊንተን አሳልፈዋል። እሳቸውም ወደ ኢትዮጵያ ተጉዘው የካርተርን ፈለግ በመከተል የራሳቸውን ሌላ ድርጅት “ክሊንተን ማዕከል” (Clinton Centre)ን አቁመው ተመልሰዋል።
ዳግማዊ ቡሽም (ፕሬዚዳንት ቡሽ) በኤድስ ጉባዔ ላይ ለመገኘት ወደ አዲስ አበባ ዘምተው ሰነባብተው ተመልሰዋል። መቼም አሜሪካንን ብዙ የሚያሳስባት ነገር አለና እነኝህ ያገለገሉ የአሜሪካ ፕሪዚዳንቶች እየተመላለሱ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሙቀት እየለኩ ማስታገሻ ፍለጋና ጥገኝነታችንን ሊያጠነክሩብን እንደሆን ግልጽ ነው።
ምሥራቅ አፍሪቃ በረሓብ በበሽታ በርስበርስ ግጭት በፖለቲካ ትርምስ እየተጠቃች ነው። የሶማልያ ጉዳይ ከራሷና ከአህጉሩ አልፎ በሕንድ ውቅያኖስ የሚንቀሳቀሱ መርከቦችን ካሰጋ ሰነበተ። የባሕር ወንበዴዎች (Pirae) ከ80 በላይ

መርከቦችን ጠልፈዋል ወይም አጥቅተዋል። መጠኑ ያልታወቀ ገንዘብ ተቀብለዋል። ታዲያ! የገንዘብ ርክክቡና ድርድሩ የሚካሂያደው በዐረብና በምዕራባውያን ከተማ መሆናቸውን ስንሰማ፤ ገንዘቡ የትኛው አገር ባንክ እንደሚቀመጥ መገመት አያዳግትም። ብዙዎቹ የገንዘብ ርክክብ በሚሥጥር ስለሚከናወኑ ለግምት ያስቸግራል።
ሶማሌዎች ነገር ስለሚገነባቸው እንጂ በምዕራብ አፍሪቃ ናይጀሪያ ጋና አካባቢ ያለው የባሕር ጠርፍና እንዲሁም በየብስ የሚደረገው ዐይን ያወጣ ውንብድና ለመረጃ (Data) ያስቸግራል እንጂ የማይተናነስ ወንጀል ይከ ናወናል። በእቅልፍ ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ “ቦኮ ሓራም” የተባለ የምዕራባውያንንና የእስልምና ኀይማኖት ተከታይ አገሮችን ግንኙነት የሚያብላሽ አዲስ አክራሪና አሸባሪ መነሳቱ ደግሞ ሌላው አሜሪካንን የሚያሳስብ ነገር ሳይሆን አይቀርም። ቦኮ ሓራም ትርፍ አልባ አክራሪ ነው። ከእምነት ጋር እንጅ ከገንዘብ ጋር ግንኙነት የለውም ቢባልም የነዳጅንም ሆነ የገንዘብን እንቅስቃሴ ማወኩ ስለማይቀር ማሳሰቡ አይቀሬ ነው። አልሻባብና የሶማሌ ፓይረቶች በብዛት የሚጠለፉት የሩቅ ምሥራቅ አገር መርከቦችን ስለሆነ የሚቀበሉት ገንዘብ ከፍተኛነት በአሁኑ የኢኮኖሚ ውድቀት ለአንዳንድ ባንኮች እንደማገገሚያም እንደማረጋጊያ ሊያገለግል መቻሉንና የሩቅ ምሥራቅ ነጋዴዎች (የመርከብ ካምፓኒዎች) ማስፈራሪያስ አይሆንም ወይ? የነ እንቶኔ ሸቅጥ ሳይጣሉ የቻይናን ትርኪምርኪ የጫነ ግዙፍ መርከብ ሕንድ ውቅያኖስን ያለምንም እንከንና ወጭ ካለፈ በሌላው የምዕራብ አገር ዕቃ ላይ የሚያመጣው ኪሣራ በ1 ዶላር አንድ ዕቃ የሚሸጠውን በ1 ዶላር አሥር ከሚሸጠው የቻይና ዕቃ ላይ የሚፈጥረው ጫና ፓይረቶቹ ለሦስት ወር መቆምና ማስለቀቂያ ተጨምሮበት ዋጋ እያረገጉ ነው። በነዳጅ ዋጋም ቢሆን የሶማሊያ ፓይረቶች የመርከብ እንቅስቃሴ ሲቆጣጠሩ የናይጀሪያዎቹ ደግሞ የሚሥጥር ቧንቧ ዘርግተው አማራጭ አቅርበዋል። ቦኮ ሓራም በሚሥጥራዊ የነጃጅ ገበያ መኖር አለመኖሩ ባይታወቅም በሽብሩ ጠንክሮአል።
በሺያት እስላሞች የሚመራው የደቡብ አፍሪቃው ፓጋድ (PAGAD) አሳሳቢ ቢሆንም የኬፕ ታውን (Gangsters) ጉልበተኛ ቡድን ዳዴ እያስኬደው በመሆኑ እንኳን አካባቢውን ተቆጣጥሮ እስልምናን በግዴታና በገንዘብ ሊያስፋፉ ኬፕታን መስጊድም ገብቶ ሰላት ለመስገድም በአላህ ጥበቃና እርዳታ ሆኖበታል። የደቡብ አፍሪቃ ፖሊስም ጸጥታ ከማስከበር ይልቅ ተስማሙ ከማለት ያለፈ የሽምግልና ሚና መጫወት እንኳ ተስኖት በተመልካችነት ተወስኗል። አሜሪካ አልሻባብን በወያኔና በአፍሪቃ ኅብረት አገሮች፤ ቦኮሓራምን በነዳጅ ገበያ፤ ፓጋድን በጋንግስተርስ.

እየተቆጣጠረ ነው። ወያኔም ነዳጅና አልማዝ ባይቸረችርም ኢትዮጵያ ያለ የሌለ የሀገሪቱ ቅርሳ ቅርስ፤ የፖለቲካ ተሰሚነት፤ መሬት፤ የሰው ኃይል (ሕፃናትና ሴቶች) እሸሸጠ/እያሻሻጠ፤ በዕርዳታ የሚያገኛቸውን ገንዘብና ቁሳቁስ እየቀነጫጨበ በምዕራባውያን ባንክ እያስቀመጠ ኢትዮጵያን (Neocolonialism) ማስገዛት ብቻ ሳይሆን አፍሪቃንም እያስማማ ነው። ከሆነለትም ከመሸጥ አይመለስም።

እንግዲህ የአሜሪካን ሃሳብና የእኛ ሃሳብ ጨርሶ አልተገናኘም። እኛ ሙሉ ነፃነት፤ እራሳችንን የማስተዳደርና ችግራችንን በራሳችን እንፍታ ስንል፤ ለችግራችሁ ደራሽ እኛ ነን፤ ብትራቡ እናቀምሳችኋልን፤ እንዳትጠግቡ እንቆጣጠራችኋለን፤ መሪ የመሾም፤ የመመልመል፤ የማሠልጠን የእኛ ተግባር ነው ይሉናል።

የተሰናባች መሪዎች ምልልስ አንዱ ምልክት ሲሆን ሽብርን ለመዋጋት የሚለው ግን የኢትዮጵያ ጉዳይ ከመስከረም 1 (911) በፊት በመሆኑ የሽብር ፖለቲካዊ ሽፋን አሜሪካኖች ሊለውጡት ይገባል። አለበለዚያ የሞኝ ዘፈን ይሆንባቸዋል። በጋዜጠኞች ለይ የሚፈጸመው ግፍና አስቂኝ ድራማ የሚያሳየን ወያኔና አሜሪካ በኢትዮጵያ ነፃ ሚዲያ መኖሩ ምን ያህል እንዳሳሰባቸውና ትልቅ ክፍተት መኖሩን የሚጠቁመን ነው። የአሽከሩ ሀጢያት መጋለጥ የጌታውን ንጽህና አያመለክትም።

ለአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያውያን የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች፤ ሰላማዊ ሰልፎች፤ ፒቲሽን፤ ሻማ ማብራት ትኩርት አልሰጣቸውም። “አውቆ የተኛ ቢጠሩት አይሰማም” ነውና አቤቱታው ወደ አሜሪካን ሕዝብ ወረድ ብሎ በመንግሥት ላይ ጫና እንዲያሳድር ማደርግ፤ በትምህርት ተቋማት፤ አቢያተ ክርስቲያናትና የኀይማኖት ተቋማት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሰብዓዊ ድርጅቶችን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን እንዲሰለፉ መሥራት የተሻለ ውጤት ያስገኛል ብዬ አምናለሁ። አሜሪካም በጉዳዩ ሊያስብበት የሚችለው በኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንካራ አመጽ አለያም በሁሉም አቅጣጫ ሲወጠር ነው።

ቸር ይግጠመን!!

ተዋናይ ከቫንኩቨር